# ለሴቶችና ወንዶች የሚቀርቡ ነጻ የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎቶች



የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎቶች እርስዎን ልጅ ስለመውለድ ወይም መቼ እንደሚወልዱ እንዲወስኑ ለመርዳት ትምህርትና ድጋፍ ያቀርቡልዎታል። አስቀድሞ ማቀድ እና ለእርስዎ ተስማሚ የሆነውን የወሊድ መቆጣጠሪያና የአኗኗር ዘይቤዎን መምረጥ በጣም አስፈላጊ የሆነው በዚህ ምክንያት ነው። ለእርስዎም ሆነ ለልጅዎ ጤና ሲባል ልጅ ከወለዱ በኋላ መልሰው ሌላ ልጅ ለማርገዝ ቢያንስ 18 ወራት መጠበቅ ይኖርብዎታል።

ለ**ነጻ** ዓመታዊ የቤተሰብ ምጣኔ ምርመራዎች፣ የወሊድ መቆጣጠሪያ ዘዴዎችና የቤተሰብ ምጣኔ ትምህርት ይመዝገቡ!

## ምንም ኮፔይ አይጠየቅም

## ለተጨማሪ መረጃ፥

**www.PlanFirst.org**
**የሚለውን ድረገጽ ይጎብኙ ወይም በ**
**Cover Virginia የነጻ ጥሪ ቁጥር**
**1-855-242-8282 ይደውሉ**
**TTY: 1-888-221-1590**

COVER VIRGINIA
የቨርጂኒያ ነዋሪዎችን
ዋጋው ተመጣጣኝ ከሆነ የጤና መድን ዋስትና ጋር የሚያገናኝ

ይህ ተቋም በፕሮግራሞቹና አገልግሎቶቹ ውስጥ ዘርን፣ ቀለምን፣ ብሔራዊ ማንነትን፣ ጾታን፣ ዕድሜን ወይም አካል ጉዳትን መነሻ አድርጎ አያገልም።
Se habla español (Spanish)

Plan First የቨርጂንያ የጋራ ብልጽግና DMAS 66E 1022 ፕሮግራም ነው

# Plan First
# የቨርጂኒያ ጥቅሙ የተወሰነ የቤተሰብ ምጣኔ ፕሮግራም



*ቨርጂኒያ ውስጥ ለሴቶችና ወንዶች የሚቀርቡ የወሊድ መቆጣጠሪያ አገልግሎቶችን የሚሸፍን ፕሮግራም*

**1-855-242-8282**
**www.PlanFirst.org**

## ለሴቶችና ወንዶች የሚቀርብ Plan First ጥቅሙ የተገደበ የቤተሰብ ምጣኔ የመድን ዋስትና

Plan First እርስዎን ጤናዎን እንዲጠብቁ ለመርዳት የቤተሰብ ምጣኔ (የወሊድ መቆጣጠሪያ ዘዴ) ዓመታዊ የአካል ምርመራዎችን እና የምርመራ አገልግሎቶችን ይሸፍናል።

የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎቶች ልጅ ስለመውለድ እና መቼ እንደሚወልዱ እንዲወስኑ ሊረዱዎ ይችላሉ።

## ምን ይሸፈናል?

- የሚከተሉትን ጨምሮ ለቤተሰብ ምጣኔ (የወሊድ መቆጣጠሪያ ዘዴ) ዓላማዎች የሚካሄዱ ዓመታዊ የአካል ምርመራዎች:
  - > PPap ምርመራዎች፣
  - > የቤተሰብ ምጣኔና በግብረ ስጋ ግንኙነት የሚተላለፍ ኢንፌክሽን (STI) የላብራቶሪ አገልግሎቶች፣
  - > የቤተሰብ ምጣኔ ትምህርትና የማማከር አገልግሎት፣
- የክርን ተቀባሪ፣ ቀለበት፣ ፓች የወሊድ መከላከያዎችን፣ IUDዎችን፣ የወሊድ መቆጣጠሪያ እንክብሎችን፣ ዲያፍራሞችን፣ ዲፖ ፕሮቬራን እና ኮንዶሞችን ጨምሮ ሁሉም በሀኪም የሚቀርቡ የወሊድ መቆጣጠሪያ ዘዴዎች*፣ እና አንዳንድ በትእዛዝ የሚሰጡ የወሊድ መቆጣጠሪያ ዘዴዎች፣ ለምሳሌ፡ የወሊድ መከላከያ ቀለበት፣ ፓች፣ የወሊድ መቆጣጠሪያ እንክብሎች እና ዲያፍራሞች፤
- ዕድሜያቸው ከ21 ዓመት በላይ ለሆኑ ግለሰቦች የሚካሄዱ የማምከን ሥነ ሥርዓቶች፣ እና
- ሽፋን ለተሰጣቸው የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎቶች የሚቀርብ የድንገተኛ ያልሆነ ትራንስፖርት

* IUDs፣ ተከላዎች እና ዴፖ ፕሮቬራ/depo provera በዶክተሩ መቅረብ አለባቸው።

**ማሳሰቢያ:Plan First የሚሸፍነው የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎቶችን ብቻ ነው።** ምን እንደሚሸፈን ለማየት እባክዎ Plan First መመሪያን ይመልከቱ ወይም **www.planfirst.org ይጎብኙ።**

## ብቁ የሚሆነው ማን ነው?

ወንዶችና ሴቶች በሚከተሉት ሁኔታዎች ብቁ ይሆናሉ

- በMedicaid ወይም FAMIS ለሚቀርቡ ሙሉ ጥቅሞች ብቁ ካልሆኑ
- የዩኤስ ዜጋ ወይም ህጋዊ ነዋሪነት ያገኙ ስደተኞች ከሆኑ
- የቨርጂኒያ ነዋሪዎች ከሆነ
- ወርሀዊ የገቢ ገደቦችን የሚያሟሉ ከሆነ ለወቅታዊ የገቢ ገደቦች እባክዎ የሚከተለውን ድረ ገጽ ይጎብኙ **www.planfirst.org**።

ዕድሜዎ ከ19 ዓመት በታች ከሆኑ ወይም ነፍሰ ጡር ከሆኑ በMedicaid ወይም FAMIS በኩል ሙሉ ጥቅማ ጥቅሞችን ለማግኘት ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ። ሌላ የግል መድን ዋስትና ሊኖርዎ እና አሁንም ለPlan First ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ። ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት **www.planfirst.org** የሚለውን ድረ ገጽ ይጎብኙ።

## የማመለክተው እንዴት ነው?

**ለPlan First ማመልከቻ ሶስት ዘዴዎች:**

- በኦንላይን በ **www.coverva.org** ያመልክቱ;
- ለCover Virginia በነጻ ጥሪ መስመር **1-(855) 242-8282 ይደውሉ** በስልክ ለማመልከት፣ ወይም
- በሚኖሩበት ከተማ ወይም ካውንቲ የሚገኘውን የአካባቢዎን የማህበራዊ አገልግሎቶች መምሪያ ይጎብኙ

ለሙሉ የMedicaid ወይም FAMIS ጥቅማ ጥቅሞች ግምገማ ይካሄድብዎታል። ለሙሉ ጥቅማ ጥቅሞች ብቁ ካልሆኑ ደግሞ ለPlan First ግምገማ ይካሄድብዎታል። የወሊድ መቆጣጠሪያ ዘዴ ካላስፈለግዎ ወይም ከዚህ በኋላ በPlan First ውስጥ መሳተፍ የማይፈልጉ ከሆነ በአካባቢዎ የማህበራዊ አገልግሎቶች መምሪያ የሚገኘውን የብቁነት ሰራተኛዎን ያነጋግሩ።

## Plan First ዶክተር የት ማግኘት እችላለሁ?

ብዙ የጤና መምሪያዎች፣ የማህበረሰብ ጤና ማዕከሎች፣ ክሊኒኮች እና የዶክተር ቢሮዎች Plan Firstን ይቀበላሉ። ለእርስዎ ቅርብ የሆነ ተሳታፊ ዶክተር ለማግኘት **www.planfirst.org** የሚለውን ድረ ገጽ ይጎብኙ።

አንዴ በPlan First ውስጥ ከተመዘገቡ በኋላ ከመረጡት ተሳታፊ ዶክተር ጋር የቤተሰብ ምጣኔ ጉብኝት ይያዙ።

በመቀጠልም ወደ ቀጠሮዎ ለመሄድ እርዳታ ማግኘት የሚፈልጉ ከሆነ የትራንስፖርት አገልግሎት ለማመቻቸት ከዚህ በታች በተመለከተው ቁጥር ይደውሉ። መደበኛ ቀጠሮ ማስያዞች ከሰኞ እስከ አርብ ከ6:00 AM እስከ 8:00 PM. ሰዓት ይከናወናሉ። እባክዎ በትንሹ ከ5 የስራ ቀናት በፊት አስቀድመው ይደውሉ።

**የትራንስፖርት ቀጠሮ ማስያዣዎች:**
**በ 1-(866)-386-8331 ይደውሉ።**

## ሌሎች የጤና እንክብካቤ ፍላጎቶች ቢኖሩኝስ?

**Plan First የሚከፍለው ለቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎቶች ብቻ ነው።** ከታመሙ ወይም የመከላከል አገልግሎቶች ወይም ሌሎች የጤና ሁኔታዎች ህክምና ማግኘት የሚፈልጉ ከሆነ ለእነዚህ አገልግሎቶች ክፍያ መክፈል ይኖርብዎታል። በገቢዎ መጠን ላይ ተመስርቶ እየቀነሰ በሚሄድ ክፍያ የመጀመሪያ እንክብካቤ ወደሚያቀርብ የማህበረሰብ ጤና ማዕከል መሄድ ይችላሉ። በቅርብዎ የሚገኘውን የማህበረሰብ ጤና ማዕከል ፈልገው ለማግኘት የሚያስችልዎ መረጃ ለማግኘት **www.hrsa.gov** የሚለውን ድረ ገጽ ይጎብኙ ወይም በ **2-1-1** ይደውሉ።

